የሰ/መ/ቁ. 41248

ሰኔ 23 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ቡርቂሶ ዋቆ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ዓቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በጋሞ አካባቢ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ክሱ አመልካች በ1996 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1/ እና 540 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ መጋቢት 09 ቀን 1997 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ሲሆን የግል ተበዳይ ሳራ ሳንቃ የተባለ ሰው ለመግደል ሞክሯል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌለ መሆኑን ገልጾ የወንጀል ድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን የክህደት ቃል ሰጥቷል፡፡ አቃቤ ሕግ በበኩሉ እንደክሱ የሚያስረዱለት የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ያሉት መሆኑን ገልፆ የግል ማስረጃዎቹን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች እንዲከላከል ተደርጎ የመከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን በማረጋገጡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት አመልካች በመከላከያ ምስክሮች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ለማስተባበል ያልቻለ መሆኑን ገልፆ አመልካችን በአቃቤ ሕጉ በኩል ተጠቅሶ በቀረበው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን አስተያየት በመቀበል እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ አመልካች ቀድሞ የወንጀል ሪኮርድ ያለበት መሆኑን አረጋግጦ በአስራ ስምንት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው የጥፋተኛነትና እና የቅጣት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች መስከረም 13 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጸሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ አቃቤ ሕግ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ውጪ ባላስረዳበት ሁኔታ በሐሰተኛ ማስረጃዎች ጥፋተኛ መባሌ ያላግባብ ነው፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም ከብዶ የተወሰነው ከወ/መ/ሕ/አንቀጽ 230 ድንጋጌ ውጪ ነው በማለት ዘርዝሮ ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ፈጸመ የተባለው የወንጀል ተግባር አንዳችም ውጤት ያላመጣ ከመሆኑ እንፃር እና አመልካች በምህረት የተለቀቀበትን ምክንያት የስር ፍርድ ቤት እንደ ቅጣት ማክበጃ ምክንያት አድርጐ በመውሰድ የአስራ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪ ሰኔ 03 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች የወንጀል ድርጊቱን አለመፈጸሙን ገልጾ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ ማስረጃ አቅርቦ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙን በሚገባ አኳኋን ማረጋገጡን የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በዚህ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታም ከግል ተበዳይ ጋር በእለቱ ከመገፈታተር ወጪ ሌላ ድርጊት የፈጸመ ስለመሆኑ አልተመሰከረም በማለት የሚከራከር ሲሆን ይህንኑ መከራከሪያ ነጥብ የሚያስረዳ መከላከያ ማስረጃ ግን በስር ፍርድ ቤት አላቀረበም፡፡ በመሆኑንም አመልካች ስለድርጊቱ አፈፃፀም በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የሚያቀርበው ቅሬታ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌ መሰረት ያለው ሥልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም እንጂ የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት ጉዳይ የማጣራት ስልጣን ካለመሆኑ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሌላው አመልካች በቅሬታ ነጥብነት ያነሳው ክርክር በሌላ የመግደል ሙከራ ተከሶ ጥፋተኛ ተብሎ በስምንት አመት ጽኑ እስራት የተቀጣበት ጉዳይ የእስራት ቅጣቱን ከመጨረሱ በፊት በይቅርታ የተፈታበትን እንደሪኰርድ ተወስዶ ቅጣቱ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎት ለአመልካች የተሰጠው ይቅርታ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ ለአመልካች የተሰጠው ይቅርታ ነው ከተባለ ይቅርታ ጽንሰ ሐሳቡና ውጤቱ ምን እንደሆነ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 230 ስር አስቀምጧል፡፡ በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር ሁለት ፓራግራፍ ሁለት መሰረት ይቅርታ ሲሰጥ በተቀጪው ላይ የተወሰነው ፍርድ ከሚያስከትለው ውጤት ጋር በወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ እንደሚኖር ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ይቅርታ የጥፋተኛነት ውሳኔ እንዳልነበረ የሚያስቆጥር አይደለም፡፡ በመሆኑም የወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ የሚኖር በመሆኑ በሪኰርድነት የማይያዝበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት  በምህረት የወጡበትን ጉዳይ በቅጣት ማክበጃነት ተጠቅመዋል በማለት ያቀረቡት ቅሬታ የስር ፍርድ ቤቱ ሊጽፈው ከፈለገው እና በትክክልም ለአመልካች የተሰጠው ይቅርታ እንጂ መህረት ያለመሆኑ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

አመልካች ተደጋጋሚ ወንጀለኛ መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች መሰረት አድርገው በአስራ ስምንት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰናቸው ስለቅጣት የተመለከቱትን አጠቃላይ መርሆዎችን ያላገናዘበ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካችን የበታች ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛ በማለት በአስራ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት መቅጣታቸው ባግባቡ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአመልካች ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡